# R E V I E W S

## የትምህርት ዓላማዎች

ከመላኩ ስብሐቱ ።

፺፩ ገጽ ፡— ዋጋው የኢት/ብር ፪ ፡—

በአያሌው ቀኖ ፤

ይህ መጽሐፍ ከሩቁ ሲመለከቱት በጥቁሩ ሽፋን ላይ በነጭ ፊደሎች የተጻፈው አርእስቱ ጉልህ ሆኖ ስለሚታይ ለማንበብ ያስጐመጃል ። ከአርእስቱም በስተቀር አንድ ዶማ ፤ አንድ ብዕር ፤ አንድ የተከፈተ መጽሐፍ በሥዕል መልክ ተደርድረው ይታያሉ ።

መጽሐፉም ሲከፈት በአምስት ምዕራፎች ተከፍሎ ይታያል ። እነዚህም ምዕራፎች ፩ኛ/ ትምህርትና ኅብረተሰብ ፤ ፪ኛ/ የሰው ልጅ እድገት ፤ ፫/ኛ የትምህርት ክፍሎች ፤ ፬ኛ/ የትምህርት ቤቶች ተግባር ፤ ፭ኛ/ የትምህርት ዓላማዎች ናቸው ።

ምንም እንኳ እነዚህ ምዕራፎች የተያያዙ ቢመስሉም ፤ ስለእያንዳንዳቸው አንድ ሰፋ ያለ መጽሐፍ መድረስ ባስፈለገ ነበር ። ይህም ማለት አንድ ደራሲ ስለብዙ ጉዳዮች ባጭሩ ጠቀስ ጠቀስ አድርጎ በአንድ አጭር መጽሐፍ ውስጥ መወያየት አይገባውም ማለት አይደለም ። ቢሆንም አንድ ደራሲ አንድ ጠቃሚ የሚመስለውን ጉዳይ መርጦ ስለዚሁ ጉዳይ በሰፊው አስተያየት ቢያቀርብ ይሻል ይሆናል ።

ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በዝርዝር ሳይሆን ፤ በጠቅላላ የአነጋገር ዘዴ ነው ። ነገር ግን ይህን ጠቅላላ አነጋገር ለመረዳት አንባቢው በቂ ዕውቀት ያለውና ደራሲው በጠቅላላ አነጋገሩ የሸፈነውን ዝርዝር ለመገመት የሚችል መሆን አለበት ። ስለዚህ ይህን መጽሐፍ አንብበው ለመረዳት የሚችሉት የሳይኮሎጂ የሶሲኦሎጂ ፤ እንዲሁም የፍልስፍና መጻሕፍትን ያነበቡ ናቸው ብዬ እገምታለሁ ። ለምሳሌ ያህል ፤ ደራሲው ካቀረባቸው አስተያየቶች የሚከተለውን እንመልከት ።

«በመልማት ላይ ያሉ አገሮች ወደኋላ የቀሩበት ሁለት የተያያዙ ምክንያቶች አሉ ።

፩/ በኑሮ ፍላጎታቸው ፤

፪/ በሥራ ዘዴያቸው ወይም በቴክኖሎጂአቸው ።

ምንም ለውጥ ባለመኖሩ ነው ። እነሆ በመልማት ላይ ያሉ አገሮች ለልማት ያላቸውን ምኞትና ፕላን ለማከናወን በኑሮ ፍላጎታቸውና በሥራ ዘዴያቸው አስፈላጊ ለውጦች መደረግ አለባቸው ። ማንም ኅብረተሰብ ድኅነትን ሊያጠፋ ስለሚችል ድኅነት ዕድላችን ነው ብለን መቀመጥ የባሰውን ድኅነት ላይ ይጥለናል ። አንድም የሥራ ዘዴ ምንም ያህል ቢሻሻል ፤ እንደገና በበለጠ ለማሻሻል ስለሚቻል አዲስ የሥራ ዘዴዎች ለማግኘት ሁልጊዜ መጣጣር ያስፈልጋል ። ይህም ሲሆን የሚችለው በትምህርት ብቻ ስለሆነ ፤ የትምህርት ድርጅቶች ይህንን ዓላማ ለማናከወን እንዲችሉ ሆነው መደራጀት አለባቸው ። »

አንዳንዶች ደራሲዎች ደግሞ እንደሚሉት እንዲያውም በመልማት ያሉት አገሮች ፍላጐታቸው በጣም ስለበዛና ከአቅማቸው ጋር ስላልተመጣጠነ በሕዝባቸው ማለት በግለሰባቸው ዘንድ የመንፈስ መረበሽ ይታያል ። የሆኖ ሆኖ ደራሲው ከላይ የሰጡት አስተያየት እንዲሁም ደግሞ በመጽሐፋቸው በአብዛኛው ገጽ ላይ እንደሚታየው በጠቅላላ አነጋገር የቀረበ እንጂ በተጨበጠ በአንድ እርግጠኛ ምሳሌ ስላልተብራራ የአስተያየቱን ትክክለኛነት መቀበል ያዳግተኛል ።

አንድ ኢትዮጵያዊ ደራሲ ስለ ብሔራዊ ጉዳዮች ለመጻፍ በሚያስብበት ጊዜ አንዱን ጉዳይ መርጦ በዚሁ ጉዳይ ላይ ለሚሰጠው አስተያየት «የአገራችንን» ፤ «የሕብረተ ሰባችንን» ፤ «የግለ ሰባችንን » ፤ ምሳሌ የተመረኮዘ ቢሆን የበለጠ ይጠቅማል ብዬ አምናለሁ ። በአሁኑ ጊዜ በጠቅላላው ስለ ሰው ልጅ እድገት ፤ ስለ ጠቅላላው የሰው ልጅ ሕብረተ ሰብና ግለ ሰብ ፤ ስለ ጠቅላላው የትምህርት ዓላማዎች መወያየት የአገራችንን ችግር የሚያቃልልንና ችግሩንም በቅርብ አጉልቶ የሚያሳየን አይመስለኝም ።